የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

**OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ሀያ ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፸፩
አዲስ አበባ ሐምሌ ፳፪ ቀን ፪ሺ፲፪

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

26th Year No.71
ADDIS ABABA July 29th, 2020

**ማውጫ**

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፲/፪ሺ፲፪

የፌደራል መንግስት ፕሮጀክቶች አስተዳደር እና አመራር ሥርዓት አዋጅ ................................፲፪ሺ፮፻፺፯

## አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፲/፪ሺ፲፪ ዓ.ም

## የፌደራል መንግስት ፕሮጀክቶች አስተዳደር እና አመራር ሥርዓትን ለመደንገግ የወጣ አዋጅ

ፕሮጀክቶችን ውጤታማ በሆነ መንገድ ተግባራዊ በማድረግ የሀገሪቱን ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ልማት እንዲያፋጥኑ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

ፕሮጀክቶች የሚመሩበትን የአሰራር ሥርዓት በህግ መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌደራል መንግስት የፕሮጀክቶች አስተዳደር እና አመራር መሰረታዊ ፅንሰ ሀሳቦችን፣ መርሆዎችን፣ ሂደቶች እና በሂደቶች ውስጥ የተለያዩ የመንግስት አስፈጻሚ አካላት

ያንዱ ዋጋ
Unit Price

**Content**

Proclamation No. 1210/2020

The Federal Government Public Projects Administration and Management System Proclamation Page ……………………………..………………12697

## PROCLAMATION NO. 1210/2020

## THE PROCLAMATION TO PROVIDE FOR THE FEDERAL GOVERNMENT PUBLIC PROJECTS ADMINISTRATION AND MANAGEMENT SYSTEM

**WHEREAS**, it has been found necessary to implement projects effectively to ensure that they accelerate the social and economic development of the country;

**WHEREAS**, it has been found necessary to legally establish the system which governs projects;

**WHEREAS**, it has been found necessary to legally determine the basic concepts, principles and processes of the administration and management of public projects of the Government of the Federal

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

ያላቸውን ሥልጣንና ኃላፊነት በህግ መወሰን አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገመንግስት አንቀፅ ፶፭ (፩) መሰረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

**ክፍል አንድ**

**ጠቅላላ**

**፩.አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "የፌደራል መንግስት ፕሮጀክቶች አስተዳደር እና አመራር ሥርዓት አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፲/፪ሺ፲፪" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪.ትርጓሜ**

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

፩/ "**ፕሮጀክቶች**" ማለት በፌደራል መንግስት ቋሚ ሀብትን ለማፍራት ወይም ለማሻሻል፣ የሀገሪቱን ኢኮኖሚ ለማሳደግ፣ የገበያ ክፍተቶችን ለመሙላት እና የቀጣዩን ትውልድ ፍትሀዊ ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ በተወሰነ ሀብት፤ ጊዜና ቦታ ምርትና አገልግሎቶችን ለመስጠት በፕሮጀክቶች አስፈፃሚ አካላት በፌደራል መንግስት በመደበኛ በጀት፣ በሀገር ውስጥና በውጭ ብድርና እርዳታ የሚከናወኑ የመንግስትን ዋስትና የሚጠይቁ ፣በመንግስት እና በግል አጋርነት ማዕቀፍ ወጪያቸው የሚሸፈን ፕሮጀክቶች ናቸው፤

Democratic Republic of Ethiopia and the duties and responsibilities of different project implementing bodies in such processes;

**NOW THEREFORE**, in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

**PART ONE**

**GENERAL**

1. **Short Title**

This Proclamation may be cited as the "The Federal Government Public Projects Administration and Management System Proclamation No. 1210/2020."

2. **Definitions**

In this Proclamation, unless the context otherwise requires:

1/ "**Project**" means investments carried out by the project implementing bodies for the acquisition or improvement of fixed assets, to accelerate economic growth, fill market failures and ensure equitable benefit of future generation , which is undertaken by limited resource, time and place or economic sectors through the regular federal government budget; projects which are being implemented through public private partnership; and projects which are being implemented by domestic and foreign loan through the Federal Government guarantee;

፪/ **"የፌደራል መንግስት ፕሮጀክቶች አስተዳደር እና አመራር ሥርዓት"** ማለት የመንግስት ፕሮጀክቶች ሀሳብ ማመንጨት፣ የፕሮጀክቶች ፅንሰ-ሀሳብ ማዘጋጀት፤ የመጀመሪያ ደረጃ መረጣ ወይም ምልመላ፤ የቅድመ-አዋጭነትና አዋጭነት ጥናት፤ የአዋጭነት ግምገማ ማድረግ፤ ቅደም ተከተል ማስያዝ፣ መምረጥ፤ በጀት ላይ መትከል፣ ትግበራ እና ድህረ ትግበራ ግምገማ መሰረታዊ መርሆች እና ዑደቶች እና የተለያዩ የፕሮጀክት አስፈፃሚ አካላት ሥልጣንና ኃላፊነት መለየትና መወሰንን የሚመራ ሥርዓት ነው፤

፫/ **"የመንግስት እና የግል አጋርነት"** ማለት በአዋጅ ቁጥር ፩ሺ፸፮/ ፪ሺ፲ አንቀፅ ፪ (፲፪) የተሰጠው ትርጓሜ ይኖረዋል፤

፬/ **"የፕሮጀክት አስፈፃሚ አካላት"** ማለት የፌደራል መንግስት ፕሮጀክቶችን በተመለከተ ከፅንሰ ሀሳብ ማመንጨት ጀምሮ እስከ ማስተዳደር ባለው ዑደት ውስጥ የሚሳተፉ የፌደራል መንግስት ፕሮጀክት አስፈፃሚ ተቋማትና የልማት ድርጅቶች ናቸው፤

፭/ **"የፕሮጀክቶች ፅንሰ-ሀሳብ"** ማለት የመነጨውን የፕሮጀክት ሀሳብ ለመወሰን ወይም ወደ ቀጣይ ኡደት ለመውሰድ በዋና ዋና መሰረታዊ የፕሮጀክት ዝግጅት መስፈርቶች መሰረት የሚዘጋጅ ሰነድ ነው፤

፮/ **"የፕሮጀክቶች የመጀመሪያ ደረጃ መረጣ ወይም ምልመላ"** ማለት የተዘጋጀውን የፕሮጀክት ፅንሰ-ሀሳብ መርምሮ ፕሮጀክቱ ወደ ቅድመ አዋጭነት ወይም አዋጭነት ጥናት ወይም በቀጥታ ወደ ቅደም ተከተል ማስያዝ፣መምረጥ እና በጀት ላይ መትከል ኡደት ሊሄዱ የሚችሉ አነስተኛ ፕሮጀክቶችን መለየትና መወሰን ነው፤

2/ "**Federal Government Public Projects Administration and Management System**" means a system in which project identification, developing project concept notes, preliminary screening, preparation of pre-feasibility and feasibility studies, appraisal of feasibility studies, prioritization, selection, budgeting, implementation and ex-post evaluation of public projects as well as identifying and determining the duties and responsibilities of different project implementing bodies is managed;

3/ "**Public Private Partnership Projects**" means projects which shall take definition specified on Article 2(12) of Public Private Partnership Proclamation No. 1076/2018;

4/ "**Project Executive Organs**" means the Federal Government Executive Organs and public enterprises which participate at any point in the cycle of projects from project identification to administration;

5/ "**Project Concept Note**" means a document prepared as per the important basic project criteria to decide on or move the project idea identified to the next phase;

6/ "**Preliminary Project Selection or Screening**" means a process of reviewing project concept notes with a view to identify and determine small projects whether they should go to pre-feasibility or feasibility studies phase or , proceed directly towards prioritization, selection and budgeting cycle;

፯/ **"የፕሮጀክቶች ዝርዝር አዋጭነት ጥናት"** የፕሮጀክቱን አዋጭነት ለመወሰን የፕሮጀክቶችን መሰረታዊ ይዘቶች ማለትም የፋይናንስ የኢኮኖሚ የማህበራዊ አዋጭነት፣የቴክኒክ አግባብነት እና አካባቢያዊ ተፅዕኖ ግምገማ በአካተተ መልክ እንደፕሮጀክቱ ባህሪ የሚከናወን ጥናት ነው፡፡

፰/ **"የፕሮጀክቶች አዋጭነት ግምገማ"** አንድ የፕሮጀክት ዝርዝር የአዋጭነት ጥናት የፋይናንስ የኢኮኖሚ የማህበራዊ አዋጭነት የቴክኒካል አግባብነት እና የአካባቢያዊ ተስማሚነት በማረጋገጥ ፕሮጀክቱ ለትግበራ ብቁ መሆን የሚደረግ ግምገማ ነው፤

፱/ **"የፕሮጀክቶች ገለልተኛ የአዋጭነት ግምገማ"** ማለት ፕሮጀክቱን ካቀረበው ወይም ከሚተገብረው አስፈፃሚ አካል ውጭ በሆነ በዚህ አዋጅ ሥልጣን በተሰጠው አካል በፕሮጀክቱ አዋጭነት ጥናት ላይ የሚደረግ የጥራት ማረጋገጫ ግምገማ ነው፤

፲/ **"የፕሮጀክት ቅደም ተከተል ማስያዝና መምረጥ በጀት ላይ መትከል"** ማለት በአዋጭነት ግምገማ መሰረት አዋጭነቱ የተረጋገጠ አዲስ የመንግስት ፕሮጀክትን ከዓመታዊ በጀት ፍላጎትና አቅርቦት አንፃር ቅድሚያ የሚያገኘውን መምረጥና ማፅደቅ ነው፤

፲፩/ **"የፕሮጀክት የትግበራ ዕቅድ"** ማለት አዋጭነቱ ተረጋግጦ፣ ተመርጦ እና ቅደም ተከተል ተይዞለት በበጀት ላይ እንዲተከል የተመረጠ ፕሮጀክት በበጀት ከመካተቱ በፊት አስፈላጊው የትግበራ ቅድመ ሁኔታ ማሟላቱን ለማረጋገጥ በአስፈጻሚ መስሪያ ቤቶች የሚዘጋጅ የፕሮጀክት ትግበራ የፊዚካልና የፋይናንስ እቅድ መርሃ ግብር ነው፤

7/ "**Project Feasibility Study**" means a research made on the nature of the project feasibility on basic nature of the projects finance, economic, social , technical qulification and environmental impact assessment to determine a project;

8/ "**Project Feasibility Appraisal**" means an appraisal undertaken to determine projects whether or not a project is viable on finance, economic, social , technical qulification and environmental assessment;

9/ "**Independent Project Review**" means a quality assurance evaluation undertaken by an independent body, other than that which proposed or will implement the project, which is mandated by this Proclamation to conduct an evaluation of the project feasibility study;

10/ "**Project Prioritization, Selection and Budgeting**" means a process of prioritizing and selecting for budgeting, a new public project which has been appraised and confirmed to be viable, based on annual budget demand and supply;

11/ "**Project Implementation Plan**" means a physical and financial implementation plan prepared by project implementing bodies for a project which has been appraised and confirmed to be viable, prioritized and selected for budgeting, in order to make sure that the necessary preconditions have been met for implementation before budgeting;

፲፪/ **“የፕሮጀክት ትግበራ”** ማለት አዋጭነቱ ተረጋግጦ በጀት የተመደበለትን የመንግስት ፕሮጀክት ምርት ወይም አገልግሎት የሚሰጥበት ደረጃ ለማድረስ የሚደረግ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ነው፤

፲፫/ **“የፕሮጀክት ክትትልና አፈፃፀም ግምገማ”** ማለት በፕሮጀክቱ የታቀዱ ተግባራት በታቀደው ጊዜ፣ ወጭ፣ መጠንና ጥራት መከናወናቸውን ለማረጋገጥ ወቅታዊ ወይም ተከታታይ የትግበራ አፈፃፀም ክትትል የሚደረግበት ሂደት ነው፤

፲፬/ **“የፕሮጀክቶች ክለሳ”** ማለት ከቁጥጥር ውጭ በሆኑ ተፈጥሯዊ እና ሰው ሰራሽ ምክንያቶች በመተግበር ላይ ያለ እንዲሁም ለትግበራ በተዘጋጀ ፕሮጀክት ላይ የሚደረግ ማንኛውንም የማስተካከያ ወይም የማሻሻያ ስራን የሚያካትት ነው፤

፲፭/ **“የፕሮጀክቶች ትግበራ ማጠናቀቂያ ግምገማ”** ማለት ፕሮጀክቱ በውል መሰረት የፕሮጀክቱ ጥራት ፣ጊዜ እና ወጪ ባስጠበቀ መልክ ተግባራዊ ተደርጎ መጠናቀቁን ለማረጋገጥ የሚደረግ ግምገማ እና የግምገማ ማጠቃለያ ሪፖርት ነው፤

፲፮/ **“የፕሮጀክት ርክክብ”** ማለት ፕሮጀክቱ ሊሰጥ የታሰበውን ምርት ወይም አገልግሎት በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ መስጠት ሲችል ወይም እሚሰጥበት ደረጃ ላይ ሲደርስ በአሰሪና ሰሪ ወይም ኮንትራክተር መካከል የሚደረግ የፕሮጀክት ርክክብ ሂደት ነው፤

፲፯/ **“የፕሮጀክቶች ድህረ ትግበራ ግምገማ”** ማለት ፕሮጀክቱ ተጠናቆ ወደ ስራ ከገባበት ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ፕሮጀክቱ የታለመለትን ዓላማ እያሳካ መሆን አለመሆኑን በመገምገም የተገኘውን ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ ለመለየት የሚደረግ ግምገማ ነው፤

12/ “**Project Implementation**” means the process of executing a project which has been appraised and confirmed to be viable and for which budget has been allocated to a stage where it can provide goods or services;

13/ “**Project Monitoring and Implementation Evaluation**” means the process of progress or conditional monitoring implementation of planned project activities to make sure that they are carried out as per the planned time, cost and quality;

14/ “**Project Revision**” means any change or modification undertaken on a project force majeure resulting from man made or natural disasters at the formulation or implementation phase;

15/ “**Project Implementation Completion Evaluation**” means an assessment carried out on aggrement focus on projects quality ,time and expenditure to verify that a project implementation has been completed and the report prepared based on such assessment;

16/ “**Project Handover**” means the process of transfer of a project from the contractor to the project owner or contractor upon the project being reaching such a stage as to partially or fully provide the intended goods or services;

17/ “**Project Post Evaluation**” means an evaluation carried out sometime after a project is completed and has become operational to assess whether or not it has achieved or is achieving its objectives and to identify the socio-economic impact it has created;

፲፰/ **"አስቸኳይ ፕሮጀክቶች"** ማለት በሰው ሰራሽና በተፈጥሮ ምክንያት የሚከሰት አደጋን ለመከላከልና ለመቋቋም በአጣዳፊነት የሚተገበሩ የመንግስት ፕሮጀክቶች ናቸው፤

፲፱/ **"የበጀት ጥሪ"** ማለት የሀገሪቱን የፊሲካልና የኢኮኖሚ ማዕቀፍ፣ ታሣቢ ተደርገው የሚወሰዱ ጉዳዮችን ባገናዘበ መልኩ የመንግስት መስሪያ ቤቶች የሚያስፈልጋቸውን ኣመታዊ በጀት አዘጋጅተው እንዲያቀርቡ በገንዘብ ሚኒስቴር የሚደረግ ጥሪ ነው፤

፳/ በወንድ ፆታ የተገለጸው አነጋገር ሴትንም ያካትታል፡፡

፫. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

፩/ ይህ አዋጅ በፕሮጀክት አስፈፃሚ አካላት በሚተገበሩ ፕሮጀክቶች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ይህ አዋጅ ለብሔራዊ ደህንነት ፣ ለሀገር መከላከያ እንዲሁም አስቸኳይ ሰው ሰራሽና የተፈጥሮ አደጋን ለመከላከል በአስፈጻሚ አካላት በሚተገበሩ ፕሮጀክቶች ላይ ተፈፃሚ አይሆንም፡፡

<u>ክፍል ሁለት</u>

<u>የፌደራል መንግስት ፕሮጀክቶች አስተዳደር እና አመራር ሥርዓት ዓላማ እና ዑደቶች</u>

፬. <u>ዓላማ</u>

ይህ አዋጅ የሚከተሉት ዓላማዎች አሉት፡-

፩/ በፕሮጀክት ዑደት ውስጥ የተለያዩ የፕሮጀክት አስፈፃሚ አካላት ያላቸውን ሥልጣንና ኃላፊነት በግልፅ በማስቀመጥ ተጠያቂነትን እና ግልፅኝነትን በማስፈን የፌደራል መንግስት ፕሮጀክቶች በታለመላቸው ጊዜ፣ ወጭ እና ጥራት ተፈፃሚ እንዲሆኑ ማድረግ፤

18/ "**Emergency Project**" means a public project implemented on an emergency basis with a view to preventing or mitigating man made or natural disasters;

19/ "**Budget Call**" means a call made by the Ministry of Finance to government offices to prepare and submit their annual budget demand taking in to account issues related to the country's fiscal and economic framework;

20/ Any expression in the masculine gender includes the feminine.

**3. <u>Scope of Application</u>**

1/ This Proclamation shall be applicable on projects which shall be implemented by project implementing bodies.

2/ Without the prejudice to the provision specified on this Article Sub article (2) of this Proclamation shall not be applicable on a National Security or National Defense projects carried out to by Executive Organ to prevent man made or natural disasters.

**<u>PART TWO</u>**

**<u>OBJECTIVE AND CYCLES OF ADMINISTRATION AND MANAGEMENT OF FEDERAL GOVERNMENT PUBLIC PROJECTS</u>**

**4. <u>Objective</u>**

This Proclamation shall have the following objectives:

1/ To ensure that projects are carried out as per the planned time, cost and quality by clearly defining the Powers and Duties of different project implementing bodies in the project cycle and by ensuring accountability and transparency;

፪/ ፕሮጀክቶች ከዝግጅት እስከ ትግበራ የሚከተሏቸው ኡደቶች እና በኡደቶች ላይ ተግባራዊ መደረግ ያለባቸውን መርሆች በግልፅ ማስቀመጥ፤

፫/ ለፕሮጀክቶች የሚመደብ ሀብት አጠቃቀምን በማጎልበት ፕሮጀክቶች የታለመላቸውን አላማ እንዲያሳኩ በማድረግ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ውጤታማነታቸውን ማረጋገጥ ነው፡፡

## ፭.ኃላፊነትና ተጠያቂነት

የእያንዳንዱ የፕሮጀክት አስፈጻሚ አካል ኃላፊ ይህ አዋጅና በአዋጁ መሰረት የሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎች በኃላፊነት በሚመራው መስሪያ ቤት ሙሉ በሙሉና በተገቢው መንገድ ተግባራዊ መደረጋቸውን በማረጋገጥ ረገድ ተጠያቂነት አለበት፡፡

## ፮. የፕሮጀክት ምደባ

፩/ማንኛውም ፕሮጀክት ከሚከተሉት ደረጃዎች በአንዱ የሚመደብ ሆኖ የምደባ ዝርዝሩን በተመለከተ የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል:-

ሀ) ከፍተኛ ፕሮጀክት፤

ለ) መካከለኛ ፕሮጀክት፤

ሐ) አነስተኛ ፕሮጀክት፤

፪/ማንኛውም የፕሮጀክት አስፈፃሚ አካል ሌሎች የአሰራር ሂደቶችን ለማስቀረት ወይም ለማለፍ ብሎ የፕሮጀክቶችን ምደባ አሳንሶ ካቀረበ ፕሮጀክቱ ውድቅ ይሆናል፤ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ፕሮጀክትን በምዕራፍ ከፋፍሎ ማቅረብ ይችላል።

2/ To clearly define the cycles that projects shall follow from formulation to implementation and the principles which shall be applicable to such cycles;

3/ To ensure that projects are socially and economically effective and achieve their objectives by optimizing the utilization of resources allocated for projects.

## 5. Responsibility and Accountability

The head of each project implementing bodies shall be accountable for ensuring that this Proclamation and Regulations and Directives issued in accordance with it are fully and properly implemented by the office he presides over.

## 6. Public Project Categories

1/ Any project shall fall under one of the following grades, the details of which shall be determined by a Regulation to be issued by the Council of Ministers:

a) Large project;

b) Medium project;

c) Small project;

2/ Notwithstanding that projects may be submitted in phases, where any project owner, with the intent of avoiding or skipping any procedures, underrepresents the grade of a project, such project shall be rejected.

## ፯. የፕሮጀክት ዑደቶች

፩/ ማንኛውም ፕሮጀክት የዝግጅት የትግበራና ድህረ ትግበራ ዑደቶች ይኖሩታል፡፡

፪/ የፕሮጀክት የዝግጅት ሂደቶች የሚከተሉት ንዑስ ኡደቶች ይኖራቸዋል፡-

ሀ) የፕሮጀክት ልየታ እና የመጀመሪያ ደረጃ መረጣ ወይም ምልመላ፤

ለ) የፕሮጀክት ቅድመ አዋጭነት እና አዋጭነት ጥናት፤

ሐ) ፕሮጀክቱ በሚመለከተው አስፈጻሚ አካል የሚደረግ የአዋጭነት ግምገማ እና የገለልተኛ የአዋጭነት ግምገማ፤

መ) ፕሮጀክቶችን ቅደም ተከተል ማስያዝ፣ መምረጥ፣ እና በጀት መትከል፤

፫/ የፕሮጀክት የትግበራ እና ድህረ ትግበራ ሂደት የሚከተሉት ንዑስ ዑደቶች ይኖረዋል፡-

ሀ) የፕሮጀክት ትግበራ ፣ክለሳ፣ አፈፃፀም ክትትል እና ግምገማ ፤

ለ) የፕሮጀክት ርክክብ ፣ የማጠቃለያ ግምገማ እና ሀብት ምዝገባ፤

ሐ) ፕሮጀክትን ወደ ምርት ወይም አገልግሎት ወደ መስጠት ማስገባት፣ እና ማስቀጠል፤

መ) የፕሮጀክቶች ድህረ ትግበራ ግምገማ፤

፬/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፪) እና (፫) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ አንድ ፕሮጀክት የፕሮጀክት ኡደቶችን ሳይጠብቅ ወደ ትግበራ እንዲገባ ሊደረግ ይችላል፤ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፡፡

## 7. Project Cycles

1/ All projects shall have the cycles of formulation, implementation and post-implementation.

2/ The formulation cycle of projects shall have the following sub-cycles:

a) Project identification and preliminary selection or screening;

b) Project pre-feasibility and feasibility study;

c) Project appraisal carried out by concerned Executive Organ project feasibility review and independent project feasibility review;

d) Project prioritization, selection and budgeting.

3/ Project implementation and post-implementation cycles shall have the following sub-cycles:

a) Project implementation, revision, monitoring and evaluation;

b) Project handover, completion assessment and assets registration;

c) Progression of project to product or service delivery and continuation;

d) Public project post evaluation.

4/ Without prejudice to Sub-articles (2) and (3) of this Article, a project may proceed to implementation without following the normal project cycles; the details which shall be further determined by a Regulation;

፭/ የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ ፬ ድንጋጌ ቢኖርም የአንድ ፕሮጀክት ፅንሰ ሀሳብ ተዘጋጅቶ ለመጀመሪያ ደረጃ መረጣ ወይም ምልመላ ቀርቦ ተቀባይነት ካላገኘ ወደ ቀጣይ ሂደት ሊሸጋገር አይችልም፡፡

፮/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፪) እና (፫) ስር የተዘረዘሩት የፕሮጀክት ዑደት ይዘት፤ መስፈርት፣ አቀራረብና አፀዳደቅን በተመለከተ ዝርዝሩ የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡

**ክፍል ሶስት**

**የፕሮጀክት የዝግጅት ዑደቶች መሰረታዊ መርሆዎች**

፰. **የፕሮጀክት ልየታ እና የመጀመሪያ ደረጃ መረጣ ወይም ምልመላ**

፩/ ማንኛውም ፕሮጀክት አስፈፃሚ አካል ላመነጨው ለውሳኔ ወይም የመጀመሪያ ደረጃ መረጣ ወይም ምልመላ በሚያግዝ መልኩ የፕሮጀክት ፅንሰ-ሀሳብ ማዘጋጀት አለበት፤

፪/ ማንኛውም ፕሮጀክት በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፯ መሰረት በፕሮጀክት የማመንጨት ሂደት መሰረታዊ ተብለው በተለዩት መስፈርቶች መሰረት ተሟልተው ሲቀርብ ብቻ ወደ መጀመሪያ ደረጃ መረጣ ወይም ምልመላ ሂደት ይገባል፡፡

፫/ ማንኛውም ፕሮጀክት ወደ ቅድመ አዋጭነት፣ ወይም አዋጭነት ጥናት፣ ወደ ቅደም ተከተል ማስያዝና ወደ መረጣ ዑደት ሊተላለፍ የሚችለው በፕሮጀክቶች ገለልተኛ አዋጭነት ግምገማ መሰረት ተቀባይነት ካገኘ ብቻ ነው፡፡



5/ Notwithstanding sub-Articles (4) of this Article, the project concept note having been developed, submitted for preliminary screening and rejected shall not proceed to the next stage or process;

6/ The details of the contents, criteria, submission and approval of the project cycles listed in Sub-articles (2) and (3) of this Article shall be determined by a Regulation to be issued by the Council of Ministers.

**PART THREE**

**BASIC PRINCIPLES OF PROJECT FORMULATION CYCLES**

**8. Project Identification and Preliminary Selection or Screening**

1/ Any project implementing body shall prepare project concept note, in a manner which would be useful for preliminary selection or screening, for project ideas identified by it.

2/ Any project shall only proceed to preliminary selection or screening when it is completed and submitted as per the basic criteria of project identification under Article (7) of this Proclamation.

3/ Any project shall only proceed to pre-feasibility or feasibility study, prioritization and selection cycles where it has been accepted through independent project feasibility review.

**፱. <u>የፕሮጀክት ቅድመ አዋጭነት እና አዋጭነት ጥናት</u>**

፩/ በመጀመሪያ ደረጃ መረጣ የተመለመለ ከፍተኛ ወይም መካከለኛ ፕሮጀክት ወደ ስራ ከመግባቱ በፊት የአዋጭነት ጥናት መደረግ አለበት፤

፪/ የፕሮጀክት አስፈፃሚ አካላት ከሀገሪቱ የሴክተር የረጅም እና መካከለኛ ዘመን እቅዶች እንዲሁም ከተለያዩ አለም አቀፋዊ ስምምነቶች በመነሳት ከፌደራል መንግስት አመታዊ በጀት ምንጮች ውጭ የፕሮጀክቶች የአዋጭነት ጥናቶችን በማከናወን ለገለልተኛ ግምገማ ማቅረብ ይችላሉ፡፡

**፲. <u>የአዋጭነት ግምገማ እና በገለልተኛ ወገን የሚደረግ የአዋጭነት ግምገማ</u>**

፩/ በፕሮጀክት አስፈፃሚ አካል የአዋጭነት ጥናት የተደረገበት ፕሮጀክት በዚህ አዋጅ ስልጣን በተሰጠው አካል ገለልተኛ የአዋጭነት ግምገማ መደረግ አለበት፡፡

፪/ የፕሮጀክት የአዋጭነት ጥናት ለገለልተኛ ግምገማ አቀራረብ የጊዜ ሰሌዳ ከዓመታዊ የፌደራል መንግስት የበጀት ጥሪ በፊት ይሆናል፤ ዝርዝሩ በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣው ደንብ መሰረት የሚወሰን ይሆናል፡፡

፫/ በገለልተኛ አካል ተገምግሞ አዋጭነቱ የተረጋገጠ ፕሮጀክት ከፌደራል መንግስት አመታዊ በጀት ጥሪ በፊት ተመርጦ ቅደም ተከተል መያዝ አለበት፡፡

፬/ አንድ ፕሮጀክት የአዋጭነት ግምገማ ተደርጎበት ሳይመረጥ እና ቅደም ተከተል ሳይዝ በበጀት ላይ አይተከልም፡፡

**9. <u>Project Pre-Feasibility and Feasibility Study</u>**

1/ A feasibility study shall be carried out for any large or medium project which has passed preliminary screening before it is implemented;

2/ Project implementing bodies may, based on the country's long term and medium-term plans for each sector as well as different International Treaties, carry out feasibility studies for projects outside Federal government annual budget sources and submit the same for independent project review.

**10. <u>Project Appraisal and Independent Project Review</u>**

1/ Any project on which a feasibility study has been carried out by any project implementing body shall be subject to an independent project review by a body authorized under this Proclamation.

2/ The time schedule for submitting project feasibility studies for independent review shall be before the Federal Government budget call and its details shall be determined by Regulation of the Council of Minister.

3/ Any project which has been reviewed by an independent body and confirmed to be viable shall be selected and prioritized before the Federal government annual budget call.

4/ A project shall not be budgeted without being appraised, selected and prioritized.

፭/ በገለልተኛ አካል የአዋጭነት ግምገማ የተደረገበት እና አዋጭነቱ የተረጋገጠ ፕሮጀክት ወደ ቅደም ተከተል ማስያዝ፣ መረጣ እና በጀት ምደባ ሂደት ይሸጋገራል፡፡

**፲፩. ፕሮጀክትን ቅደም ተከተል ማስያዝ፤ መረጣ እና ፕሮጀክቱን በበጀት ላይ ስለ መትከል**

የፕሮጀክት መረጣ፣ ቅደም ተከተል ማስያዝ እና በጀት ላይ መትከል በሚከተሉት መልክ ይከናወናል፡-

፩/ በአዋጭነት ግምገማ አዋጭ ተብሎ የተለየ ፕሮጀክትን በጀት ለመመደብ የሀገሪቱን የብድር ጫና፤ የማክሮ ኢኮኖሚው ሁኔታ እና ሌሎች ጉዳዮችን ባማከለ መልኩ ፕሮጀክትን በመምረጥና ቅደም-ተከተል በማስያዝ በበጀት ላይ እንዲተከል ምክረ ሀሳብ ይቀርባል፤

፪/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ ፩ መሰረት ተመርጠውና ቅደም ተከተል ይዘው የቀረቡትን ፕሮጀክቶች፤ በመካከለኛ ዘመን የበጀት ማዕቀፍ እና በአመታዊ በጀት ውስጥ እንዲካተቱ ይደረጋል፤

፫/ ተመርጠው ቅደም ተከተል ይዘው በአመታዊ በጀት ውስጥ የተካተቱ ፕሮጀክቶች በየደረጃቸው ለሚመለከታቸው አካላት መቅረብ እና መፅደቅ አለባቸው፤

፬/ በፕሮጀክት አስፈፃሚ አካላት በሀገር ውስጥ እና በውጭ ብድር የሚከናወኑ ፕሮጀክቶች አዋጭነታቸው ተገምግሞ ሲረጋገጥ ብቻ ተግባራዊ መደረግ አለባቸው፡፡

5/ Any project which has been reviewed by an independent body and confirmed to be viable shall move to prioritization, selection and budgeting.

**11. Public Project Prioritization, Selection and Budgeting**

Project selection, prioritization and selection shall be carried out as follows:

1/ In order to allocate budget for a project which has been appraised and identified as viable, a project shall be selected and prioritized and recommended for budgeting taking into consideration the country's debt burden, macro-economic conditions as well as other factors;

2/ Projects selected, prioritized and recommended as per Sub-article (1) of this Article shall be included in the medium-term budget framework and annual budget;

3/ Projects which have been selected, prioritized and included in the annual budget shall be submitted to the appropriate bodies at different levels for approval;

4/ Projects considered to be implemented by domestic and foreign loan shall be reviewed by an independent body and confirmed to be viable shall proceed to implementation.

## ክፍል አራት

## የፕሮጀክት የትግበራ እና ድህረ ትግበራ ዑደቶችና መሰረታዊ መርሆዎች

### ፲፪. የፕሮጀክት ትግበራ፣ መከለስ፣ አፈፃፀም ክትትል እና ግምገማ፤

፩/ ማንኛውም ፕሮጀክት ሲተገበር አካባቢያዊ፣ ሀገራዊና ዓለም አቀፋዊ ህጎችን፣ ስታንዳርዶችንና ቅደም ተከተሎችን ባማከለ መልኩ መሆን አለበት፤

፪/ ከፕሮጀክት መደበኛ ክትትል በተጨማሪ ፕሮጀክቱ ከደረሰበት አፈፃፀም ደረጃ አኳያ በዋናነት የፕሮጀክቱ አፈፃፀም ፶ በመቶ ወይም በመካከለኛ ዘመን እንዲሁም ፕሮጀክቱ ተጠናቆ ርክክብ በሚካሄድበት ወቅት መገምገም ይኖርበታል፤

፫/ እንደ ፕሮጀክት ውስብስብነት እና የትግበራ መርኃ ግብር ርዝመት በአንዳንድ የፌደራል መንግስት ፕሮጀክቶች ላይ የመካከለኛ ዘመን ግምገማ ይዘት ያለው ተጨማሪ ግምገማ በፕሮጀክት ትግበራ ዘመን ሊከናወን ይችላል፤

፬/ የፕሮጀክቱ ወሰን የተቀየረ ከሆነ፣ በፕሮጀክቱ ላይ ከቁጥጥር ውጭ በሆኑ የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ክስተቶች ምክንያት ፕሮጀክቱን መከለስ የሚያስገድድ ሁኔታ ከተፈጠረ የፕሮጀክት ክለሳ ሊፈቀድ ይችላል፡፡

፭/ አንድ ፕሮጀክት በግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር ፯፻፵፱/፪ሺ፩ መሰረት ክለሳ ማድረግ ከተፈቀደው መጠን በላይ የዋጋ ጭማሪ የሚያስፈልገው ከሆነ ፕሮጀክቱ ተዘጋጅቶ በድጋሚ የአዋጭነት ግምገማ ተደርጎበት መከለስ ይኖርበታል፤

፮/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፭) መሰረት የክለሳ ጥያቄ ቀርቦበት በድጋሚ በሚደረግ የአዋጭነት ግምገማ መሰረት ተቀባይነት ያገኘ ፕሮጀክት ለውሳኔ ሰጭ አካላት ቀርቦ መፅደቅ አለበት፡፡

## PART FOUR

## PROJECT IMPLEMENTATION AND POST-IMPLEMENTATION CYCLES AND BASIC PRINCIPLES

### 12. Project Implementation, Revision, Monitoring and Evaluation

1/ Any project shall be implemented in a manner that takes into consideration Local, National and International Laws, Standards and priorities.

2/ In addition to the regular project monitoring, based on its progress, any project shall mainly be evaluated up on 50% completion or mid-term and upon completion and handover.

3/ Subject to the complexity and implementation schedule of the project, an additional evaluation similar to mid-term evaluation may be carried out on certain projects during the project implementation period.

4/ Project revision may be allowed where there is a change in the scope of the project or force majeure resulting from acts of nature or man-made circumstances occur which necessitate revision of the project.

5/ Where a project requires a cost increase beyond the amount which is allowed for revision under the Ethiopian Government Procurement and Property Administration Proclamation No. 649/2009, such project shall be reformulated and reappraised again in order to be revised.

6/ Any project for which a request for revision is submitted and has been appraised and accepted again as per Sub- article (5) of this Article shall be submitted to the appropriate decision-making bodies for approval.

**፲፫. <u>የፕሮጀክት ርክክብ፣ የማጠቃለያ ግምገማ እና የሀብት ምዝገባ</u>**

የፕሮጀክት ርክብብ ሂደት ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው የኮንትራት ውል መሰረት መከናወናቸውን በሚያረጋግጥ መልኩ መከናወን አለበት፡፡

**፲፬. <u>ፕሮጀክት ወደ ምርት ወይም አገልግሎት ማስገባት እና ስለ ማስቀጠል</u>**

፩/ ተጠናቆ ርክክብ የተደረገበት ፕሮጀክት ወደ ስራ ለማስገባት እና ለማስቀጠል የቅድመ ዝግጅት ስራዎች በታቀደ መልክ መከናወን አለባቸው፡፡

፪/ መንግስት አንድን ፕሮጀክት ወደ ምርት ወይም አገልግሎት ማስገባት የሚያስችል በጀት በወቅቱ የመመደብ ኃላፊነት አለበት፡፡

**፲፭. <u>የፕሮጀክት ድህረ ግምገማ</u>**

በተመረጡ ፕሮጀክቶች ላይ የፕሮጀክቶች ድህረ ትግበራ ግምገማ ፕሮጀክቶች ተጠናቀው ወደ ስራ ከገቡ ቢያንስ ከ ፪ ዓመት ቢበዛ በ፲ ዓመት በማይበልጥ ጊዜ ውስጥ መከናወን አለበት፡፡

**፲፮. <u>የፕሮጀክት መረጃ አያያዝ እና አስተዳደር</u>**

ማንኛውም ፕሮጀክት አስፈፃሚ አካል የሚከታተለውን ፕሮጀክት ከፅንሰ ሀሳብ ጀምሮ እስከ ትግበራ ድረስ ያለውን መረጃ በመደበኛነት ደህንነቱ በተረጋገጠ የመረጃ ቋት የመያዝ ሀላፊነት አለበት፡፡

**<u>ክፍል አምስት</u>**

**<u>በፕሮጀክት ዑደቶች ላይ የፕሮጀክት አስፈፃሚ አካላት ሥልጣንና ኃላፊነት</u>**

**፲፯. <u>የወል ሥልጣንና ተግባራት</u>**

በሌላ ህግ የተሰጣቸው ሥልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ እያንዳንዱ የፌደራል መንግስት ፕሮጀክት አስፈፃሚ አካል፡-



**13. <u>Project Handover, Completion Assessment and Assets Registration</u>**

The projects handover shall be carried out by ensuring project completion on a manner in accordance with the agreement.

**14. <u>Moving a Project to Production or Service Provision and Continuation</u>**

1/ Works of preparation shall be carried out in a planned manner to move a project which has been completed and handed over to operation and continuation.

2/ The Government shall be responsible for allocating the budget necessary to move a project to production or service provision on time.

**15. <u>Project Post Evaluation</u>**

Project post evaluation shall be carried out on selected projects at least 2 years and not more than 10 years after the project has been completed and have become operational.

**16. <u>Management and Administration of Project Information</u>**

Any project implementing body shall be responsible for keeping in a safe database, on a regular basis, project information starting from concept note to implementation for projects it monitors.

**<u>PART FIVE</u>**

**<u>THE POWERS AND DUTIES OF PROJECT IMPLEMENTING BODIES IN PROJECT CYCLES</u>**

**17. <u>Common Powers and Duties</u>**

Without prejudice to the Powers and Duties given to them under other legislations, each project implementing body shall:

፩/ በስራው መስክ ወይም በስሩ በሚገኝ ተቋም የመነጨ ፕሮጀክት ፅንሰ-ሀሳብ እና የአዋጭነት ጥናት በሚዘረጋ የአሰራር ስርዓት መሰረት አዘጋጅቶ ያቀርባል፤

፪/ የአዋጭነት ጥናት የተደረገበትን ፕሮጀክት በራሱ አቅም የአዋጭነት ግምገማ በማካሄድ ጥራቱን ያረጋግጣል፤

፫/ የፕሮጀክት አዋጭነት ጥናት እንዲደረግበት ለተወሰነ አነስተኛ ፕሮጀክት በገለልተኛ አካል የአዋጭነት ግምገማ በማስደረግ የአዋጭነት ግምገማ ሪፖርት ለፕላንና ልማት ኮሚሽን እና ለገንዘብ ሚኒስቴር ያቀርባል፤

፬/ በህግ በተፈቀደው መጠን ውስጥ ላሉ ውሳኔ የተሰጠባቸውን ፕሮጀክቶች ክለሳ የሚያስፈልጋቸውን ክለሳ በማድረግ ለገንዘብ ሚኒስቴር ለውሳኔ ያቀርባል፤

፭/ በህግ ከተፈቀደው በላይ ክለሳ ለሚጠይቅ ፕሮጀክት የክለሳ ጥያቄ በማዘጋጀት ለፕላንና ልማት ኮሚሽን ለግምገማና ውሳኔ ያቀርባል፤

፮/ ለአዋጭነት ግምገማ የሚቀርብ እና ተግባራዊ እንዲሆን ውሳኔ የተሰጠበት ፕሮጀክት ከመተግበሩ በፊት የትግበራ ቅድመ ሁኔታዎች ማሟላቱን ያረጋግጣል፤

፯/ ተመርጦ ቅደም ተከተል ለተያዘለት ፕሮጀክት የአዋጭነት ጥናትን መሰረት በማድረግ የፕሮጀክት ትግበራ እቅድ በማዘጋጀት ለምክረ ሀሳብ ለፕላንና ልማት ኮሚሽን ያቀርባል፤

1/ Prepare and submit a concept note and feasibility study for any project identified in its area of work or by an entity under it in accordance with the system established;

2/ Conduct, in its own capacity, an appraisal and quality assurance on projects for which a feasibility study has been carried out;

3/ Have an appraisal carried out, by an independent body, for small projects for which a feasibility study is required, and submit the feasibility study report to the Planning and Development Commission and the Ministry of Finance;

4/ With regard to approved revisions of projects the amounts of which are within the limit set under the law, carryout the necessary revision and submit the same to the Ministry of Finance for Approval;

5/ With regard to requests for project revision which are beyond the limit set under the law, prepare a request for revision and submit such request to the Planning and Development Commission for reviewing and approval;

6/ Make sure that the necessary preconditions for implementation have been met before a project which has been submitted for appraisaland has been approved for implementation;

7/ Prepare a project implementation plan, based on their feasibility study, for projects which have been selected and prioritized, and submit the same to the Planning and Development Commission for recommendation;

፰/ በፕሮጀክት ዝግጅት፣ አዋጭነት ግምገማ፣ ትግበራና ክትትል ሁደት በተሰጣቸው ስልጣን መሰረት ፤

ሀ) የፕሮጀክት አስፈላጊ መጠቀሚያዎችና መገልገያዎች መኖራቸውን ያረጋግጣል፣ ይፈቅዳል፣ ይወስናል፣ ይገመግማል፣ ይቆጣጠራል፤

ለ) የፕሮጀክት የአገልግሎት እና የመሰረተ ልማት ስታንዳርዶች ያወጣል፣ በስራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፤

፱/ በአመታዊ በጀት ውስጥ ለተካተተ ፕሮጀክት በቅድም ተከተል ማስያዝ ወይም በበጀት በሚካተትበት ወቅት የቀረበውን የትግበራ እቅድ አሻሽሎ የመጨረሻ የሆነውን የትግበራ እቅድ የበጀት ዓመቱ በተጀመረ በመጀመሪያው ወር ለገንዘብ ሚኒስቴርና ለፕላን እና ልማት ኮሚሽን ያቀርባል፤

፲/ በስሩ ተግባራዊ እየተደረገ በሚገኝ ፕሮጀክት ላይ የመደበኛ ክትትል እና ግምገማ ያደርጋል፣ የፕሮጀክት አፈፃፀም ሪፖርት ለገንዘብ ሚኒስቴር እና ለፕላንና ልማት ኮሚሽን ያቀርባል፤

፲፩/ ከፍተኛ ወይም መካከለኛ ፕሮጀክትን በተመለከተ የሚመለከታቻውን ተቋማት በማሳተፍ በዋና ዋና የትግበራ ምዕራፎች የአፈፃፀም ግምገማ ያደርጋል፤

፲፪/ በስሩ ወይም በተጠሪ ተቋማት ስር ያለ ፕሮጀክት ሲጠናቀቅ የማጠናቀቂያ ሪፖርት በማዘጋጀት ለፕላንና ልማት ኮሚሽን እና ለገንዘብ ሚኒስቴር ያቀርባል፤

8/ As per the powers given to them with regard to the process of formulation, appraisal, implementation and monitoring of projects:

a) Make sure that essential project tools are available and approve, decide on, evaluate and supervise the same;

b) Issue project service and infrastructure standards and ensure their implementation;

9/ Prioritize Government Projects which have been included in annual budget or revise the implementation plan submitted upon their inclusion in annual budget and submit the final implementation plan to the Ministry of Finance and the Planning and Development Commission within one month of the commencement of the budget year;

10/ Carry out regular monitoring and evaluation of projects which are being implemented under it; submit the project progress report to the Ministry of Finance and the Planning and Development Commission;

11/ With regard to large and medium projects, carryout project implementation evaluations at major implementation phases by engaging the appropriate bodies;

12/ Upon completion of any project under it or bodies accountable to it, prepare a project completion report and submit the same to the Planning and Development Commission and to the Ministry of Finance;

፲፫/ አንድን ፕሮጀክት በተገባለት ውል መሰረት የታለመለትን አላማና ውጤት በሚያሳካ መንገድ መጠናቀቁን አረጋግጦ ይረከባል፤ ፕሮጀክቱ ወደ ምርት ወይም አገልግሎት መስጠት እንዲገባ ያደርጋል፤

፲፬/ በስሩ የሚገኝ የፕሮጀክት ሀብትን ይመዘግባል፣ ለሚመለከተው የመንግሰት አካል ወቅታዊ የሆነ መረጃ ያቀርባል፤

፲፭/ ተግባራዊ የተደረጉ ከፍተኛ እና መካከለኛ ፕሮጀክቶችን በተመለከተ እንደ አስፈላጊነቱ የድህረ ትግበራ ግምገማ ያከናውናል፣ በድህረ ትግበራ ግምገማ የተገኙ ግብዓቶችን በቀጣይ ለሚተገበሩ ፕሮጀክቶች ዝግጅት ጥቅም ላይ መዋዋላቸውን ያረጋግጣል፤

፲፮/ ፕሮጀክቶች በሀገር አቀፍ ደረጃ በተሟላ ሁኔታ በመረጃ ቋት እንዲያዙ የፕሮጀክት አፈፃፀም መረጃዎች ለፕላንና ልማት ኮሚሽን ያቀርባል፤

፲፯/ በስሩ ወይም በተጠሪ ተቋማት ስር ያሉ ፕሮጀክቶችን በተመለከተ ውል በሚያዘጋጁበት ወይም በሚዋዋሉበት ጊዜ ከህግ አንፃር በፌደራል ጠቅላይ ዓቃቤ ህግ ተገቢውን አስተያየትና ምክር እንዲሰጥበት ያደርጋል፤

፲፰/ በሀገር ውስጥ እና በውጭ ብድር በፌደራል መንግስት ዋስትና የሚከናወኑ ፕሮጀክቶች በዚህ አዋጅ የተደነገጉትን የፕሮጀክቶች ዑደቶች ጠብቀው መዘጋጀታቸውን ተግባራዊ መደረጋቸውን ያረጋግጣል፡፡

13/ Take over projects by confirming that they have been completed in accordance with the project agreement and in a manner which meets the target objectives and outcomes, and move such projects to production or service delivery;

14/ Register the assets of projects under it; provide up to date information to the appropriate Government Body;

15/ Ensure projects with regard to large and medium projects which have been implemented, carry out ex-post evaluation as necessary; use inputs gathered during such ex.post evaluation for new project formulation;

16/ Submit project implementation information to the Planning and Development Commission so that projects can be included in a comprehensive national database;

17/ Upon drawing up or signing agreements regarding projects under it or bodies accountable to it, make sure that the Federal Attorney General provides the appropriate legal comments and recommendations on them;

18/ Ensure projects which are considered for implementation through domestic and foreign loan mechanism by the federal government guarantee follow the project cycles specified in this proclamation during formulation and implementation.

**፲፰. የፕላን እና ልማት ኮሚሽን ሥልጣንና ተግባራት**

፩/ በፕሮጀክቶች አስፈፃሚ አካላት የሚቀርብ የፕሮጀክት ፅንሰ-ሀሳብ ይዘትን በመገምገም የመጀመሪያ ደረጃ የግምገማ ውሳኔ ይሰጣል፤

፪/ በመካከለኛ እና ከፍተኛ ፕሮጀክቶች ላይ የገለልተኛ አዋጭነት ግምገማ ያደርጋል፤

፫/ የአዋጭነት ጥናት እንዲከናወንበት በመጀመሪያ ደረጃ መረጣ ውሳኔ የተሰጠበት አነስተኛ ፕሮጀክት ላይ በፕሮጀክቶች አስፈፃሚ አካላት የቀረበው አዋጭነት ግምገማ ደረጃውን የጠበቀ መሆኑን ያረጋግጣል፣

፬/ የአዋጭነት ግምገማ ተደርጎባቸው አዋጭነታቸው የተረጋገጡ አዳዲስ ፕሮጀክቶች ወደ ካፒታል በጀት እንዲገቡ በሀገሪቱ የልማት ዕቅድ እና በገንዘብ ሚኒስቴር በሚሰጠው ሙያዊ ምክር መሰረት ይመርጣል፤ ቅደም ተከተል በማስያዝ ምክረ ሀሳብ ለገንዘብ ሚኒስቴር ያቀርባል፤

፭/ በመካከለኛ እና የረዥም ዘመን የልማት ዕቅድ ክትትልና ግምገማ ማዕቀፍ በተመረጡ ስትራቴጂክ ፕሮጀክቶች ላይ ክትትልና ግምገማ ያደርጋል፣ በፕሮጀክት አፈፃፀም ላይ የታዩ ምርጥ ተሞክሮዎችን በመቀመር የልምድ ልውውጥ ያደረጋል፣ ተግባራዊ መደረጋቸውን ያረጋግጣል፤

፮/ መካከለኛና ከፍተኛ ፕሮጀክቶች ሲከለሱ በህግ ከተደነገገው በላይ በፕሮጀክቱ በጀት ላይ ለውጥ የሚያስከትሉ ሲሆን የአዋጭነት ግምገማ በማድረግ ምክረ ሀሳብ ለገንዘብ ሚኒስቴር ያቀርባል፤

**18. Powers and Duties of the Planning and Development Commission**

1/ Reviewing the content of concept notes submitted by project implementing bodies and giving initial appraisal decision ;

2/ Carrying out independent feasiblity review on medium and large projects;

3/ With regard to small projects which have passed preliminary screening, ensuring that the appraisal report submitted by project implementing bodies is up to standard;

4/ Selecting and prioritizing for inclusion into capital budget, as per the country's development plan and the expert advice given to it by the Ministry of Finance, new projects which have been appraised and confirmed to be viable, and submitting a recommendation to the Ministry of Finance with regard to the same;

5/ Carrying out monitoring and evaluation of selected strategic projects under the medium-term and long-term development plan monitoring and evaluation framework; organizing best practices observed in project implementation, conducting experience sharing and ensuring their implementation;

6/ Where the revision of a medium or large project would result in changes in the project budget which are beyond the limit set under the law, carrying out project appraisal and submitting a recommendation to the Ministry of Finance;

፯/ እንደ አስፈላጊነቱ የፕሮጀክት ዝግጅት፣ አዋጭነት ግምገማና ማፅደቅ፣ ትግበራ ሂደት የሚያስፈልጉ ሙያዊና ቴክኒካዊ ጉዳዮች ተሟልተው እንዲገኙ ሁኔታዎችን ያጠናል፣ ይወስናል፣ ያስተባብራል፣

፰/ የፕሮጀክት ፅንሰ ሀሳብ፣ አዋጭነት ጥናት፣ አዋጭነት ግምገማ፣ የትግበራ ዕቅድ፣ አፈፃፀም ክትትልና ግምገማ፣ ክለሳ እና ድህረ ትግበራ ግምገማን በሚመለከት መመሪያዎች ያወጣል፣ በፕሮጀክት ኡደት ውስጥ መመሪያዎቹ በአግባቡ ተፈፃሚ መሆናቸውን ያረጋግጣል፣

፱/ ፕሮጀክቶችን የሚመለከቱ ማዕከላዊ የመረጃ ቋት የሚደራጁበትን፣ የሚጠናቀሩበትና የሚሰራጩበት ስርዓትና ይዘት ከገንዘብ ሚኒስቴር ጋር በመሆን ያዘጋጃል፣ ይወስናል፣ ተግባራዊነታቸውን ይከታተላል፣

፲/ ዋና ዋና የፕሮጀክቶች መረጃዎች ተደራሽ በሆኑ የመገናኛ አግባቦች ድህረ ገጾችን ጨምሮ ወቅታዊነታቸውን ጠብቀው ለህዝብ ይፋ እንዲሆን ያደርጋል፣

፲፩/ በፕሮጀክቶች አስተዳደር እና አመራር ዙሪያ እንደ አስፈላጊነቱ የአቅም ግንባታ ተግባራትን ያከናውናል፣

፲፪/ በመንግስትና በግል አጋርነት እንዲከናወኑ የታቀዱ ፕሮጀክቶች ወደ ዝግጅትና ትግበራ ሂደት ከመግባታቸው በፊት ከሀገሪቱ የመካከለኛ እና የረዥም ጊዜ የልማት ዕቅዶች ጋር የተጣጣሙ መሆኑን ያረጋግጣል፣ ሆኖም በዚህ አግባብ የሚተገበሩ ፕሮጀክቶች መረጣ፣ የአዋጭነት ጥናት፣ ግምገማ፣ ውሳኔ አሰጣጥ እና ትግበራ በአዋጅ ቁጥር ፩ሺ፸፮/፪ሺ፲ መሰረት ተግባራዊ የሚደረግ ይሆናል፡፡



7/ Carrying out, approving and coordinating studies to make sure that the necessary professional and technical preconditions have been met for formulation, feasibility appraisal and implementation of projects;

8/ Issuing Directives regarding project concept notes, feasibility studies, project appraisals, implementation plans, progress monitoring and evaluation; revision and post evaluation; ensuring that such Directives are properly implemented in project cycles;

9/ Developing, approving and monitoring the implementation of a central database system, and the content thereof, for organizing, compiling and disseminating project related information in collaboration with the Ministry of Finance;

10/ Publicize the main projects information on widespread channels including the webpages;

11/ Carrying out capacity building activities related to project administration and management as necessary;

12/ It shall ensure public private partnership projects are in accordance with the medium-term and long-term development plan of the country before it advances to formulation and implementation. Notwithstanding this selection, appraisal approval and implementation of such projects shall be carried out in accordance with Proclamation No. 1076/2018.

## ፲፱. የገንዘብ ሚኒስቴር ሥልጣንና ተግባራት

፩/ በፕሮጀክት ፅንሰ ሃሳቦች ላይ የመንግስት ፕሮጀክቶች ፋይናንስ ለማድረግ አቅም መኖሩን ለማረጋገጥ በፕላንና ልማት ኮሚሽን ለሚቀርብ ጥያቄ ምክረ ኃሳብ ወይም ውሳኔ ይሰጣል፤

፪/ የፕላን እና ልማት ኮሚሽን በአዋጭነት ግምገማ አዋጭ ተብለው ለበጀት ዕጩ የሆኑ ፕሮጀክቶችን ለመምረጥ እና ቅደም-ተከተል ለማስያዝ እንዲችል የሀገሪቱን የፋይናንስ ሁኔታ፣ የብድር ጫና እና ሌሎች ማክሮ ኢኮኖሚ ሁኔታዎችን መሰረት በማድረግ ሙያዊ ምክር ይሰጣል፤

፫/ ከፕላን እና ልማት ኮሚሽን የሚቀርብን የፕሮጀክቶች የቅደም ተከተል ምክረ ሀሳብና የትግበራ ዕቅድ መሰረት በማድረግ አዳዲስ ፕሮጀክቶች በጀት ውስጥ እንዲካተቱ ያደርጋል፣ በየደረጃው እንዲጸድቁ ይከታተላል፤

፬/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፫) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በሚኖረው ተጨባጭ የፋይናንስ ሁኔታ አንፃር የፕሮጀክቶች የማሸጋሸግ ስራ ሊሰራ ይችላል፤

፭/ ፕሮጀክቶች በረቂቅ አመታዊ በጀት በሚካተቱበት ወቅት የቀረበው የትግበራ እቅድ ከመጀመሪያ ደረጃ ክፍያ በፊት ተሻሽሎ የመጨረሻ የትግበራ እቅድ መቅረቡን ይገመግማል፤ ያረጋግጣል፣

፮/ በህግ በተፈቀደው መጠን በፕሮጀክቶች አስፈፃሚ አካላት በፕሮጀክት ክለሳ ላይ የሚቀርብ ማሻሻያ ላይ ውሳኔ ይሰጣል፤

## 19. Powers and Duties of the Ministry of Finance

1/ Providing timely recommendation or decision with regard to requests made by the Planning and Development Commission regarding project concept notes to determine whether there is capacity to finance public projects;

2/ Providing expert advice based on the country's financial conditions, debt burden and other macro-economic conditions in order to enable the Planning and Development Commission to select and prioritize projects which have been appraised, confirmed to be viable and eligible for budgeting;

3/ Based on the project prioritization recommendation and the implementation plan submitted by the Planning and Development Commission, ensuring that new projects are included in the budget, and monitoring their approval at different levels;

4/ Without prejudice to Sub-article (3) of this Article, projects may be reprioritized taking actual financial conditions into consideration;

5/ Reviewing and confirming that the implementation plan submitted when projects were included in the draft annual budget is revised and the final implementation plan is submitted before initial payment is made;

6/ Approving project revisions submitted by Executive Organ within the amount allowed under the law;

፯/ በህግ ከተፈቀደው በላይ በፕሮጀክቶች አስፈፃሚ አካላት በሚቀርብ የመካከለኛ ወይም ከፍተኛ ፕሮጀክቶች ክለሳ ላይ የፕላንና ልማት ኮሚሽን በሚያቀርበው የውሳኔ ሀሳብ መሰረት ተፈፃሚ ያደርጋል፤

፰/ የፕሮጀክቶችን ፋይናንስ በበላይነት ያስተዳድራል፣ ተግባራዊ እየተደረጉ የሚገኙ ፕሮጀክቶችን በፕሮግራም በጀት ማዕቀፍ መደበኛ የአፈፃፀም ክትትልና ግምገማ ያደርጋል፤ የተጠቃለለ መደበኛ የፌደራል መንግስት ፕሮጀክቶች አመታዊ የአፈፃፀም ክትትል ሪፖርት ለሚመለከታቸው የመንግስት አካላት በመደበኛነት ያቀርባል፤

፱/ ሀገራዊ የፕሮጀክቶች ሀብት አመዘጋገብ መረጃ ቋት እንዲኖር ያደርጋል፤ በፕሮጀክቶች ባለቤቶች የሚያዙ የፕሮጀክቶች ሀብት ምዝገባ መረጃዎችን እንዲያዝ ያደርጋል፤

፲፩/ የመንግስት ፕሮጀክቶችን የፊዚካል እና የፋይናንስ አፈፃፀም መረጃ በማጠናከር በፕሮጀክቶች መረጃ ቋት ውስጥ እንዲገቡ ያደርጋል፤

፲፪/ የፕሮጀክቶች ርክክብ፣ ስራ ማስኬጃን፣ ጥገና እና ሀብት ምዝገባ ሂደት እና መርሆችን በተመለከተ መመሪያ ያወጣል፡፡

## ፳. የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ሥልጣንና ተግባራት

፩/ በኮንስትራክሽን ፕሮጀክት አስተዳደር መስክ ቴክኒካል ጥናቶችን ያከናውናል፤

፪/ ዘመናዊ የኮንስትራክሽን የፕሮጀክት አስተዳደር ሥርዓትን በተመለከተ ማንዋሎችን በማዘጋጀት ተደራሽ ያደርጋል፤ በስራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፤ የአቅም ግንባታ ስራዎችን ያከናውናል፤



7/ Implementing the recommendations of the Planning and Development Commission with regard to project revisions beyond the amount allowed under the law submitted by Executive Organ for medium or large projects;

8/ Supervising project finance, carrying out regular monitoring and evaluation on projects that are being implemented under the program budget framework, and regularly submitting a general annual progress monitoring report of projects to the appropriate government bodies;

9/ Ensuring that there is a national project assets registration database; maintaining project assets registration data kept by project owners;

10/ Ensuring that the physical and financial progress information of projects is compiled and entered in the projects' database;

11/ Issuing a Directive on the processes and principles of handover, operation, and maintenance and assets registration of public projects.

## 20. Powers and Duties of the Ministry of Urban Development and Construction

1/ Carrying out technical studies on the administration of construction projects;

2/ Preparing and making available systems and manuals on modern construction project administration and ensuring that they are applied; carrying out capacity building works;

፫/ የኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶች የዲዛይን ስታንደርድ ያወጣል፣ የአዋጭነት እና የዲዛይን ጥናት በኮንስትራክሽን ዲዛይን መሰረት መደረጉን ያረጋግጣል፣ ከኮንስትራክሽን ስታንዳርድ አኳያ ቁጥጥር ያደርጋል፤

፬/ የኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶች ላይ የኮንስትራክሽን ኦዲት ያደርጋል፡፡

**፳፩. <u>የፌደራል ግዥ እና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ስልጣንና ተግባራት</u>**

የፕሮጀክት ኮንትራክተር፣ አማካሪ፣ ግዥ፣ የጨረታ ዝግጅት፣ መረጣ እና ማፅደቅ አፈፃፀምን በተመለከተ ፣ ማንዋሎች በማዘጋጀት ለሚመለከታቸው የፕሮጀክቶች አስፈፃሚ አካላት ተደራሽ ያደርጋል፣ በስራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፤ ይቆጣጠራል፤ ይወስናል፡፡

**፳፪. <u>የፌደራል መንግስት የተቀናጀ የመሰረተ ልማት ማስተባበሪያ ኤጀንሲ ሥልጣንና ተግባራት</u>**

፩/ የፕሮጀክት አስፈፃሚ አካላት በመሰረተ ልማት ፕሮጀክቶች ላይ በሚያቀርቡት የፕሮጀክት ጥናት መሰረት ፕሮጀክቶች ወደ ትግበራ ከመግባታቸው በፊት አስፈላጊ የመሰረተ ልማት ፋሲሊቲዎች መቀናጀታቸውንና መሟላታቸውን ያረጋግጣል፤ ይወስናል፤ ይከታተላል፤

፪/ የመሰረተ ልማት ፕሮጀክት ትግበራ ላይ በመሰረተ ልማት አቅራቢ ድርጅቶች መካከል ሊኖር የሚገባውን ቅንጅት እና አሰራር በተመለከተ ሙያዊ ምክር ይሰጣል፤ ቅንጅቱን በበላይነት ይመራል፤ ይከታተላል፤ ይወስናል፤

3/ Issuing construction project design standards; ensuring that feasibility and design studies are carried out in accordance with such construction design standards; carrying out monitoring in accordance with the construction standards;

4/ Carrying out construction audits on construction projects.

**21. <u>Powers and Duties of the Public Procurement and Property Administration Agency</u>**

The Public Procurement and Property Administration Agency shall prepare, make available to the appropriate project implementing bodies, ensure and supervise the implementation of, and approve and manuals regarding the procurement of project contractors and consultants and the preparation, selection and awarding of bids.

**22. <u>Powers and Duties of the Federal Government Integrated Infrastructure Development Coordinating Agency</u>**

1/ Based on the project documents submitted by infrastructure projects, ensuring, approving and monitoring that the necessary infrastructural facilities are integrated and fulfilled before projects proceed to implementation;

2/ Providing expert advice regarding the integration and coordination which should exist between infrastructure provider companies during implementation of infrastructure projects; supervising, monitoring and approving such integration;

፫/ በመሰረተ ልማት ፕሮጀክቶች ላይ ለሚነሱ የወሰን ማስከበር እና የካሣ ክፍያ ጥያቄዎች የሚስተናገዱበትን የአሰራር ሥርዓት ይዘረጋል፡፡

**፳፫ የፌደራል ጠቅላይ ዓቃቤ ህግ ሥልጣንና ተግባራት**

የመንግስት ፕሮጀክቶች ፈፃሚ አካላት በስራቸው ያሉ ፕሮጀክቶችን በተመለከተ ውል በሚያዘጋጁበት ጊዜ ከህግ አንፃር ተገቢውን አስተያየትና ምክር ይሰጣል፣ የሕዝብና የፌደራል ፕሮጀክቶች አስፈፃሚ አካላት ጥቅም ይጎዳል ብሎ ሲያምን የውል ዝግጅትና ድርድር ከተቋማቱ ጋር በመሆን ያደርጋል፤

**፳፬. በፌደራል መንግስት ፕሮጀክቶች ላይ የፌደራል መንግስት እና ክልሎች ግንኙነት**

የፌደራል መንግስት እና ክልሎች በፌደራል መንግስት ፕሮጀክቶች ላይ በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ በትብብር ይሰራሉ፡-

፩/ ለፕሮጀክቶች መሬት ማቅረብ፤
፪/ በፕሮጀክቶች ምክንያት ለሚነሱ ማህበረሰቦች በአግባቡና በህግ መሰረት ካሣ መከፈሉን ማረጋገጥ፤
፫/ በፕሮጀክቶች ዝግጅት እና ትግበራ ሂደት የአካባቢው ማህበረሰብ ተሳታፊ መሆኑን ማረጋገጥ፤
፬/ ፕሮጀክቶች ትግበራ ሂደት በፕሮጀክቱና በህብረተሰቡ መካካል የሚነሱ አለመግባባቶችን መፍታት፤
፭/ በፕሮጀክት አፈፃፀም መረጃ መሰረት በፕሮጀክቱ አካባቢ ለሚኖሩ ማህበረሰቦች ስለፕሮጀክቶቹ ግንዛቤ ማስጨበጥ፡፡

3/ Prepare a system for handling issues related right of way and compensation raised with regard to Federal Government infrastructure projects.

**23. Powers and Duties of the Federal Attorney General**

It shall, where Government Institutions prepare agreements related to projects that are under them, provide the appropriate legal advice and recommendation and, where it believes that public interest and the interests of government offices are at stake, prepare and negotiate agreements in collaboration with the respective government office.

**24. The Relationship between the Federal Government and Regional States with Regard to Federal Government Public Projects**

The Federal Government and Regional States shall work collaboratively on Federal Government public projects with regard to the following matters:

1/ Providing land for projects;
2/ Ensuring that proper compensation is given as per the law to communities displaced due to projects;
3/ Ensuring that local communities participate in the formulation and implementation of projects;
4/ Addressing disputes between projects and communities in the process of implementing Federal Government public projects;
5/ Creating awareness for local communities living in project areas about the project as per the project progress information.

## ክፍል ስድስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**፳፭.ደንብ ስለማውጣት**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ለአዋጁ አፈፃፀም የሚረዳ ደንብ ሊያወጣ ይችላል፤

**፳፮. ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች**

ይህን አዋጅ የሚቃረን ማንኛውም ሕግ ወይም የአሰራር ልምድ በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚ አይሆንም፤

**፳፯. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ**

ይህ አዋጅ ከመፅናቱን በፊት ወደ ትግበራ የገባ ፕሮጀክት ሲሰራበት በነበረው ስርዓት መሰረት ፍፃሜ ያገኛል፡፡

**፳፰. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሐምሌ ፳፪ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም.**

**ሳህለወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ**

**ሪፐብሊክ ፕሬዝደንት**

## PART SIX

## MISCELLANEOUS PROVISIONS

**25. Issuing of Directives**

The Council of Ministers may issue Directive which is necessary for the implementation of the Proclamation.

**26. Non-Applicable Laws**

No law or practice inconsistent with this Proclamation shall have effect with respect to matters provided for in this Proclamation.

**27. Transitory Provisions**

The implementation of a project which was started before the effective date of this Proclamation shall be completed in accordance with the system under which it was being implemented.

**28. Effective Date**

This Proclamation shall enter into force on the date of its publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa On the July 29th Day of 2020.**

**SAHLEWORK ZEWDE**

**PRESDIENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC**

**REPUBLIC OF ETHIOPIA**